www.chilot.me

3ኛ ዓመት ቁጥር 1
3th Year No. 1

ሐረር ሐምሌ 27 ቀን 1990
Harar August 3/1998

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

## HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| ያንዱ ዋጋ 1:00 | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 7/1990
የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 7/1990------------------ ገጽ 34

## በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 7/1990 ዓ.ም

የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ለከተማው ነዋሪ ሕዝብ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነትና ብልጽግና ለማስገኘትና ወደ ተሻለ የኑሮ ደረጃና እድገት ለማራመድ ከፍተኛ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመረዳት

የማዘጋጃ ቤቱን የገቢ ምንጭ በማስፋፋት፣ ድርጅታዊ ብቃቱንና አስተዳደሩንም በማሻሻል የከተማው እድገት በዕቅድ እንዲመራ ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በማዘጋጃ ቤቱና በሥራና ከተማ ልማት ቢሮ እንዲሁም በቀበሌዎች መካከል ሊኖር የሚችለውን የሥራ ግንኙነት በአዲስ መልክ መደንገግ በማስፈለጉ፣

በአዲሱ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ መሠረት የከተማ ቦታን የኢንቨስት-መንት በሚያመች መልኩ ማስ ተዳደር አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት፣

በሐረሪ ሕዝብ ክልል ህገ-መንግሥት አንቀፅ 26/2/ሀ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

www.chilot.me



## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 7/1990 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

1. «ህገ-መንግሥት» ማለት የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ህገ-መንግሥት ነው።
2. «ምክር ቤት» ማለት የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ነው።
3. «ቢሮ» ማለት የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ማለት ነው።
4. «ማዘጋጃ ቤት» ማለት የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ነው።
5. «የከተማ ሹም» ማለት የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤትን በበላይ ኃላፊነት እንዲመራ በክልሉ መንግሥት የሚሾም ባለሥልጣን ነው።
6. «ካዳስተር» ማለት በከተማ ክልል ለግብር አተማመን በመሬት ይዞታ ላይ የሚደረግ የዋጋ የመጠንና የባለቤትነት ይፋዊ ምዝገባ ወይም ጥናት ነው።
7. «ጠፍ እንስሳ» ወይም «ንብረት» ማለት ባለቤት የሌለው እንስሳ ወይም ንብረት ወይም ባለቤት እያለው ስድ ሆኖ ማዘጋጃ ቤቱ በሚሰይማቸው የህዝብ መገልገያ ስፍራዎች ላይ የተለቀቀ እንስሳ ነው።
8. «የሥነ-ሥርዓት አስከባሪ» /ተቆጣጣሪ/ ማለት ማዘጋጃ ቤቱ ለሕዝብ አገልግሎት እንዲሰጡ በሰየማቸው የከተማ በታዎች ላይ የጽዳት ጉድለት ባልተፈቀደ በታ የንግድ እንቅስቃሴ በሚያከናውኑ፣ ህገ-ወጥ ግንባታ በሚያከናውኑ ወዘተ . . . ተከታትሎ እርምጃ የሚያስወስድ አካል ነው።

### 3. የአዋጁ ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ ተፈጻሚ የሚሆነው በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሐረር ከተማ ላይ ብቻ ይሆናል።

### 4. ሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት የራሱ አርማ ይኖረዋል።

/ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።/

www.chilot.me



## ምዕራፍ ሁለት

### 5. የማዘጋጃ ቤቱ አደረጃጀትና ተጠሪነት

1. የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት አላማውን ለማስፈጸም ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ይኖሩታል።

2. ማዘጋጃ ቤቱ በክልሉ መንግሥት ምክር ቤት በሚሾም የከተማ ሹም የሚመራ ሆኖ ተጠሪነቱ ለክልሉ ለሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ይሆናል ተገቢ ለሆኑ ጉዳዮች ከክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ድጋፍ ያገኛል።

### 6. የማዘጋጃ ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ መሠረት የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

1. የክልሉ ምክር ቤት በሚያወጣው ህግ መሠረት የቦታ ኪራይ፣ የአገልግሎት ታክስ የንግድ ግብር፣ የቤት ግብርና ቀረጥ ይሰበስባል በገቢውም ይተዳደራል።

2. የከተማው እድገት በማስተር ፕላኑ መሠረት መመራቱን ያረጋግጣል፣ የካርታና የቅየሳ ሥራዎች በተገቢው መንገድ ይሰራል፣ የከተማ ቦታዎች በደረጃ ይመደባል፣

3. በተገቢው መንገድ ለመኖሪያና ለድርጅት መሥሪያ የሚሆኑ ቦታዎች ይሸነሽናል፣ በጨረታ ወይም በምሪት ያከፋፍላል የይዞታ ማስረጃ ምስክር ወረቀትና የቤት ፕላን እንዲሁም ቤት የመሥራትና የማደስ ፍቃድ ይሰጣል።

4. በከተማው ማስተር ፕላን መሠረት አዳዲስ መንገዶችን ይሰራል፣ ነባሮችንም ይጠግናል የመንገድ መብራት እንዲሁም የወስጥ ተፋሰሶችን በአግባቡ እንዲሰሩና እንዲያዙ ያደርጋል፣

5. ለከተማው መሠረታዊ የሕዝብ መገልገያ ቦታዎችን፣ የመኖሪያና የንግድ ቤቶችን፣ ፓርኮችን፣ የገበያ ቦታዎችን፣ የመንገድ አትክልቶችን፣ የሕዝብ መናፈሻዎችን፣ የከብት መገበያያ ቦታዎችን፣ የመቃብር ቦታዎችን ቄራዎችን ይሰራል፣ ያደራጃል፣ ይጠብቃል ያከራያል ይንከባከባል።

6. ስለ ከተማው ውበትና ጽዳት አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፣

7. እያንዳንዱ ግለሰብ፡ ቤተሰብ ወይም ድርጅት የሚሰራውና የሚያሰራውን ሥራ ሁሉ የሕዝብ ጤንነትና ደህንነት፣ ፀጥታ፣ የማያውክ መሆኑን በሚመለከተው አካል ያረጋግጣል ይቆጣጠራል።

8. የአካባቢው ጤንነትና ንፅህናን በተመለከተ ከሚመለከታቸው ቢሮዎች

www.chilot.me



ጋር በመተባበር አስፈላጊውን ትምህርት ይሰጣል፣ ቁጥጥር ያደርጋል፣ እርምጃ ይወስዳል

9. የእሳት አደጋ መከላከያ አገልግሎት ይሰጣል፤

10. በከተማው ውስጥ በመንገዶች ለመተላለፍ የሚያውከውን ወይም እንቅፋት የሚሆነውን ጠፍ እንስሳ ወይም ንብረት ወይም ማናቸውንም ነገር ይከላከላል፣ ያስወግዳል።

11. በከተማው ውስጥ የሚቀርቡ ቦታ ነክ ውዝግቦች፣ የቤት ባለቤትነትና መሰል አቤቱታዎችን በመጀመሪያ ደረጃ ያስተናግዳል።

12. የካዳስተር የፕላን ለውጥና የድር ጅት ቦታ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ በሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ሲፈቀድም ስራ ላይ ያውላል፤

13. የከተማውን ፕላን በመከተል ህገ ወጥ ግንባታዎችን እንዳይሰሩ ይከላከላል፤ የማፍረስ ሥራዎች እንዲፈጸሙ ያደርጋል፤

14. የማዘጋጃ ቤቱን ሥልጣንና ተግባር ለማስፈጸም የራሱን ሥነ-ሥርዓት አስከባሪ ተቆጣጣሪ ያደራጃል፤

7. <u>የከተማው ሹም ሥልጣንና ተግባር</u>

የከተማው ሹም ተጠሪነቱ ለክልሉ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ሆኖ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

1. ማዘጋጃ ቤቱ በሕግ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ሥራ ላይ ያውላል፤

2. የማዘጋጃ ቤቱን የልማት ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ በሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ያፀድቃል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤

3. ስለ ማዘጋጃ ቤቱ የወጡ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤ ይከታተላል፤ ያረጋግጣል

4. በመንግሥት ሠራተኞች ሕጎችና ደንቦች መሠረት ሠራተኞችን ያስተዳድራል፤

5. የማዘጋጃ ቤቱ ገቢዎች በታሪፍ መሠረት በወቅቱ መሰብሰባቸውንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤ የግብር ምደባ በወቅቱ እንዲካሄድ የገቢ ምንጮች የሚስፋፉበት ሥልት እንዲቀየስ ያደርጋል።

6. የተመደበበትን የማዘጋጃ ቤት ሥራዎች በሚገባ ለማካሄድ የሚያስችለውን ሕግና ደንብ ረቂቅ አዘጋጅቶ በሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በኩል ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል ሲጸድቅም በሥራ ላይ ያውላል፤

7. በማዘጋጃ ቤቱ ስለሚከናወኑት ሥራዎች ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፤

www.chilot.me



8. በተጨማሪም ከቢሮው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

## ምዕራፍ ሶስት

### 8. ማዘጋጃ ቤቱ የቀበሌ መስተዳደርችን በመከተል ስለሚኖረው ሥልጣንና ተግባር

የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት የቀበሌ መስተዳደሮችን በተመለከተ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. ቀበሌዎች ከቤት ኪራይና ከልማት ተቋማት የሚሰበስቡትን ገቢ በተከፈተላቸው የባንክ አካወንት ገቢ ማድረጋቸውን ያረጋግጣል፤ የሂሳብ አያያዝና አጠቃቀማቸውንም ይቆጣጠራል፤ እንደሁኔታውም መመሪያ ይሰጣል።

2. የቀበሌዎችን የሥራ ዕቅድና በጀት ገምግሞ ያጸድቃል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

3. የቀበሌዎች ገቢ የሚጠናከርበትን ዘዴ ይቀይሳል በሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ሲጸድቅም ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

4. የቀበሌ መስተዳደሮች ከልዩ ልዩ አገልግሎት ከሚሰበሰቡትና ለማዘጋጃ ቤቱ ፈሰስ ከሚደረጉት ገንዘብ እንደ አስፈላጊነቱ እየታየ ለቀበሌዎች ድጎማ ያደርጋል፤

5. የቀበሌ መስተዳደሮች የሥራ ክንውን ሪፖርት በየጊዜው እንዲያቀርቡ ያደርጋል።

## ምዕራፍ አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 9. የቀበሌ መስተዳደሮች ማዘጋጃ ቤቱን በተመለከተ ስለሚኖራቸው ግዴታና ኃላፊነት

ቀበሌዎች ከማዘጋጃ ቤቱ የሚሰጡ መመሪያዎች፤ ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የመስጠትና የመቀበል ግዴታ አለባቸው

### 10. ተፈጻሚነት

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፤ ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተመለከቱት ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም።

### 11. ዝርዝር ደንብ የማውጣት ሥልጣን

ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም እንደአስፈላጊነቱ ማዘጋጃ ቤቱ ዝርዝር የአፈጻጸም ደንብና መመሪያ በማመንጨት በሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በኩል ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ

www.chilot.me



ያቀርባል፣ ሲጸድቅም በሥራ ላይ ያውላል፣

12/ <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ይህ አዋጅ በሥራ ላይ እንዲውል የክልሉ መንግሥት አስፈጻሚ አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

13/ <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ሐረር ሐምሌ 27 ቀን 1990 ዓ.ም

አብዱላሂ ኢድሪስ

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ

መንግሥት ፕሬዝዳንት